መልእክት ሦስት

## የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁለቱ ክፋቶች
## እና ኢኮኖሚውን ለመፈጸም የእግዚአብሔር ታማኝነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኤር. 2፥13፤ መዝ. 36፥8-9፤ ዮሐ. 4፥10፣ 14፤ 7፥37-39፤ 1ቆሮ. 10፥4፤ 12፥13

**I. የእስራኤልን ኃጢአት እና የእግዚአብሔርን ቁጣ፣ ተግሳጽ እና ቅጣት በሚመለከት ንግግር የተሞላው የኤርሚያስ መጽሐፍ እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ያለው ውጥኑ ለመገለጡ የሆነች የእግዚአብሔር ሙላት ትሆን ዘንድ ቤተ ክርስቲያንን፣ የእግዚአብሔርን አምሳያ፣ እንደ የእግዚአብሔር መጨመር፣ እንደ የእግዚአብሔር መተለቅ፣ ለማፍራት በሆነ ግብ ለእርካታቸው እና ለድሰታቸው ወደ መረጣቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ለማደል የሕያው ውኃዎች መፍለቂያ፣ ምንጭ መሆኑን ይገልጣል፤ የመለኮታዊው መገለጥ ማዕከላዊው እና ዋናው ነገር እግዚአብሔር ሕይወታችን እና ሁሉ ነገራችን ይሆን ዘንድ ራሱን እኛ ውስጥ መሥራት ለሆነው ዓላማ እኛን መፍጠሩ እና መዋጀቱ ነው—2፥13፤ መዝ. 36፥8-9፤ ዮሐ. 3፥29-30፤ 4፥10፣ 14፤ 7፥37-39፤ ራእ. 7፥17፤ ኤፌ. 3፥16-19፦**

- ሀ. በትንሣኤ የሆነው የሕይወት ውኃ ከእርሱ ወጥቶ ወደ ተዋጁት ሕዝቡ ውስጥ ይፈስ እና ይጠጡ ዘንድ ክርስቶስ እንደ ሕያዉ መንፈሳዊው ዓለት በእግዚአብሔር ሕግ ስልጣን ተመትቷል—ዘጸ. 17፥6፤ 1ቆሮ. 10፥4።
- ለ. በትንሣኤ ካለው ከአንዱ መንፈስ መጠጣታችን የአካሉ ክፍሎች ያደርገናል፤ እንደ አካሉ ይገነባናል፣ የክርስቶስ ሙሽራ እንድንሆንም ያዘጋጀናል—12፥13፤ ራእ. 22፥17።

**II. "ሕዝቤ ሁለቱን ክፉ ነገሮች አድርገዋልና እኔን የሕያውን ውኃ ምንጭ ትተውኛል፣ የተቀደዱትንም ጉድጓዶች፣ ውኃውን ይይዙ ዘንድ የማይችሉትን ጉድጓዶች፣ ለራሳቸው ቆፍረዋል"—ኤር 2፥13፦**

- ሀ. እንደ እርሱ መገለጥ የእርሱ መጨመር ይሆኑ ዘንድ የእስራኤል ሕዝብ እንደ የሕያው ውኃዎች ምንጭ ከእግዚአብሔር ሊጠጡ ይገባ ነበር፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ሁለት ክፉ ነገሮች አደረጉ፦
  1. እግዚአብሔርን እንደ መፍለቂያቸው፣ እንደ ምንጫቸው ትተው ከእግዚአብሔር ውጪ ወደ ሆነ ወደ ሌላ ምንጭ ዘወር አሉ፤ እነዚህ ሁለት ክፉ ነገሮች መላውን የትንቢተ ኤርሚያስ መጽሐፍን ይገዛሉ።
  2. ጉድጓዶችን መቆፈር የሚያሳየው እግዚአብሔርን ለመተካት የሆነ ነገር (ጣዖታትን) ለመሥራት በሰው ጉልበት የሆነን ድካምን ነው።
  3. ጉድጓዶቹ የተቀደዱ መሆናቸውና እና ውኃ መያዝ አለመቻላቸው የሚጠቁመው እግዚአብሔር ራሱ እንደ ሕያው ውኃ ወደ እኛ ውስጥ ከመታደሉ በስተቀር የትኛውም ነገር ጥማችንን ሊያረካ እና ለመገለጡ የእግዚአብሔር መጨመር ሊያደርገን እንደማይችል ነው—ዮሐ. 4፥13-14።
- ለ. በእግዚአብሔር ዓይኖች ክፉ እና በደለኛ የሆነው ከእርሱ ለመጠጣት ወደ እርሱ የማይመጣ ሰው ነው (ኢሳ. 55፥7)፤ የክፉዎች ክፋት ጌታን ለሙብላት፣ ለመጠጣት እና ለመደሰት ወደ ጌታ አለመምጣታቸው ነው፤ ብዙ ነገሮች ያደርጋሉ፣ ነገር ግን ጌታን ለመንካት፤ እርሱን ለመውሰድ፤ እርሱን ለመቀበል፤ እርሱን ለመቅመስ እና እርሱን ለመደሰት አይመጡም፤ በእግዚአብሔር እይታ፣ ከዚህ የበለጠ ክፉ ነገር የለም (57፥20-21፤ ተዛ. 55፥1-2)።
- ሐ. እግዚአብሔር ይተልቅ ዘንድ ራሱን እንደ የሰው እርካታ ወደ ሰው ውስጥ ለማደል ወጥኗል፣ ነገር ግን ሰው ከዳተኛ እና አመንዝራ ሆነ ለጣዖታት ሲልም እግዚአብሔርን ተው፦
  1. በልባችን ያለ ጣዖት (ሕዝ. 14፥3) በእኛ ውስጥ ያለ ከጌታ በላይ የምንወደው እና እንደ ውድ መዝገብ የምንቆጥረው የትኛውም ነገር እና በሕይወታችን ጌታን የሚተካ ነገር ነው (1 ዮሐ. 5፥21)፦
     - ሀ. ጣዖታትን በልባቸው የሚያኖሩ በጣዖታታቸው በኩል ከእግዚአብሔር ተለይተዋል (ሕዝ. 14፥5)።
     - ለ. በውስጣቸው ጣዖታት ያሏቸው ነገር ግን በውጫዊ መንገድ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሁሉ ሊያገኙት አይችሉም (ቁ. 3፤ ተዛ. ኤር. 29፥13)።
  2. ጣዖታትን በማምለካቸው፣ የእስራኤል ሕዝብ ራሳቸውን ከንቱ እና ምንም አደረጉ፤ የጣዖታታቸው ቁጥር እንደ ከተሞቻቸው ቁጥር የሆኑ እጅግ ብዙ ጣዖታት ነበሯቸው (2፥5፣ 28፤ 11፥13)፤ የእስራኤል ሕዝብ የአምላካቸውን እውነታ፤ ክብራቸውን በጣዖታት ከንቱነት ለወጡ (2፥11፤ መዝ. 106፥20፤ ሮሜ 1፥23)።
  3. ክህደት የእግዚአብሔርን መንገድ መተውና ከእግዚአብሔር ውጪ የሆኑ ነገሮችን ለመከተል ሌላ መንገድ የመውሰድ ጉዳይ ነው፤ እግዚአብሔርን መተውና ወደ ጣዖታት መዞር ነው—ኤር 2፥19።
  4. የእስራኤል ሕዝብ በባቢሎናውያን በተማረኩ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ያኔም ቢሆን ጣዖታታቸውን አልተዉም ከመልካሚቷ ምድርም ወደ ባቢሎን ተሸከመዋቸው መውሰድ ነበረባቸው፤ የትኛውም እግዚአብሔርን

የሚተካ ወይም የእግዚአብሔርን ስፍራ የሚይዝ ነገር ሁሉ ለአምላኪው ሽክም የሚሆን ጣዖት ነው—ኢሳ. 46፡1።

5. ዲዳ፣ ድምጽ የሌላቸው ጣዖታት (1ቆሮ. 12፡2፤ ዕን. 2፡18-20) አምላኪዎቻቸውን ዲዳ እና ድምጽ የሌላቸው ያደርጋሉ፣ ነገር ግን ሕያዉ አምላክ አምላኪዎቹን በእርሱ መንፈስ እንዲናገሩ ያደርጋቸዋል (1ቆሮ. 12፡3፤ መዝ. 115፡4-8፤ 2ቆሮ. 4፡13፤ መዝ. 116፡12-13)፦
   ሀ. የትኞቹም የእግዚአብሔር አምላኪዎች ዝም ማለት የለባቸውም፤ ሁሉም በእግዚአብሔር መንፈስ "ኢየሱስ ጌታ ነው" ብለው ለመናገር ድምጻቸውን መጠቀም አለባቸው።
   ለ. ይህ—"ኢየሱስ ጌታ ነው" ብሎ መናገር—የሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች ዋና ሥራ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ውስጥ ለመሳተፍ፤ ለመደሰት እና ለመለማመድ መንገዱ ተገቢ በሆነ መንፈስ የጌታን ስም መጥራት ነው—1ቆሮ. 12፡3፤ ተዛ. ሮሜ 14፡17።
   ሐ. "አቤቱ፣ ሙታን የሚያመሰግኑህ አይደሉም፣ ወደ ሲኦልም የሚወርዱ ሁሉ፤ እኛ ሕያዋን ግን ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔርን እንባርካለን ። ሃሌሉያ"—መዝ. 115፡17-18።
6. እኛ ያለን የትኛውም ነገር እና እኛ የሆንነው የትኛውም ነገር ጣዖት ሊሆን ይችላል፤ የእስራኤል ሕዝብ ለጣዖታት ሲሉ እግዚአብሔርን በመተዋቸው ክፉ እና ከሀዲ ነበሩ፤ እንዲህ ባለው ለእግዚአብሔር ባለመታመን ጉዳይ፣ እኛም ከእስራኤል ጋር አንድ ዓይነት ነን።

## III. ኢኮኖሚውን ለመፈጸም የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማየት አለብን—ተዛ. 37፡3፦

ሀ. ምንም እንኳን እኛ ያልታመንን ብንሆንም እግዚአብሔር ታማኝ ነው (ሰቆ. 3፡23)፤ አንድ ታወቂ የሆነ የመዝሙር አዝማች (የእንግሊዝኛው የመዝሙር መጽሐፍ ላይ #19) እንዲህ ይላል "ታማኝነትህ ብዙ ነው! ታማኝነትህ ብዙ ነው! / ማለዳ ማለዳ አዳዲስ ምህረቶችን አያለሁ።/ የሚያስፈልገኝን ሁሉ እጅህ ሰጥቶኛል፤ / ታማኝነትህ ብዙ ነው፣ ጌታ ሆይ፣ ለእኔ!"።

1. ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እና ይህ መዝሙር የሚለውን ፍጥረታዊ በሆነ መንገድ ወይም መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ልንረዳው እንችላለን።
2. የእግዚአብሔርን ታማኝነት ፍጥረታዊ በሆነ መንገድ ከተረዳነው፣ የእርሱ ታማኝነት በዋናነት በቁሳዊ አቅርቦቶች ወይም በአካላዊ በረከቶች ጉዳይ እንደሆነ ልናስብ እንችላለን፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ታማኝነት በፍጥረታዊ መረዳታችን መሠረት አይደለም፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡9 እኛን ወደ ልጁ ኅብረት ውስጥ በመጥራቱ እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ ይናገራል፣ ነገር ግን ለፍጥረታዊው መረዳታችን እርሱ ለደህንነታችን በመጠንቀቅ ታማኝ የሆነ ላይመስል ይችላል።
3. "የሐዋርያው ጳውሎስን መከራዎች አስቡ። በእግዚአብሔር ተጠርቷል፣ ተልዕኮ ተሰጥቶታል፣ ሸክም ተሰጥቶታል፣ ተልኳልም፣ ነገር ግን በሄደበት ሁሉ ችግሮች ነበሩበት። ለምሳሌ ያህል፤ ክርስቶስን መስበክ እንደጀመረ ወዲያውኑ በስደት መሰቃየት ጀመረ። በቅጥር ላይ በቅርጫት በመውረድ ከደማስቆ ማምለጥ እንኳን ነበረበት። ይህ ማለት እግዚአብሔር ለጳውሎስ ታማኝ አልነበረም ማለት ነውን? አይደለም፣ ይህ ማለት የእግዚአብሔር ታማኝነት በፍጥረታዊ መረዳታችን መሠረት አይደለም ማለት ነው።" (*Life-study of Jermiah*, p. 28)—ሐዋ. 9፡15-16፣ 23-25፤ 2 ቆሮ. 11፡30-33፤ ቆላ. 1፡24፤ 2 ቆሮ. 1፡5፤ ፊልጵ. 3፡10፤ ራእ. 1፡9፤ 2 ጢሞ. 2፡10፤ 3፡12።
4. ወደ ጌታ ኢየሱስ ውስጥ ስናምን፣ ውጫዊ ሰላም እና በረከት እንዲኖረን ጠብቀን ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን በዚህ ፈንታ ብዙ ችግሮች ገጥሞን ሊሆን ይችላል፤ ደህንነታችንን፣ ጤናችንን፣ ወይም ንብረቶቻችንን አጥተን ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ክርስቲያኖች እንዲህ ያሉ ነገሮችን ሲለማመዱ፣ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ሊከትቱ እና መከራዎች በእነርሱ ላይ እንዳይደርሱ ለምን እንዳልከለከለ ሊጠይቁ ይችላሉ—ሐዋ. 14፡22፤ 1 ተሰ. 3፡2-5።
5. ችግሮች እንዲደርሱብን በመፍቀዱ፣ እግዚአብሔር እኛን ከጣዖታት በማዞር እና ወደ ራሱ መልሶ በማምጣት በዓላማው ታማኝ እንደሆነ መገንዘብ አለብን። ሰላማችን፣ ደህንነታችን፣ ጤናችን እና ንብረቶቻችን ጣዖታት ሊሆኑብን ይችላሉ፣ ነገር ግን እንደ የሕያው ውኃዎች ምንጭ ከእርሱ እንጠጣ ዘንድ እነዚህን ነገሮች ለማስወገድ እግዚአብሔር ታማኝ ነው።
6. ለምሳሌ፣ ቤታችን ወይም ንብረቶቻችን ጣዖታት ከሆኑብን፣ ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከእነርሱ እንጠጣለን፤ የእግዚአብሔር ታማኝነት እነዚህን ጣዖታት የማስወገድ እና ከእርሱ እንድንጠጣ የማድረግ ጉዳይ ነው—መዝ. 36፡8።

7. እግዚአብሔር እኛን ወደ ኢኮኖሚው በመምራት ታማኝ ነው (1 ቆሮ. 1፡9፤ 1 ተሰ. 5፡23-24)፣ ኢኮኖሚውም እኛ ክርስቶስን እንድንጠጣው፣ ክርስቶስን እንድንበላው፣ ክርስቶስን እንድንደሰተው፣ ክርስቶስን እንድንመጥጠው እና ከእኛ ጋር እንዲዋሐድ ነው፤ ይህም ኢኮኖሚውን ለመፈጸም እግዚአብሔር በእኛ መጨመሩን ያገኘ ዘንድ ነው።
8. እኛ ከእስራኤል የተሻልን እንዳልሆንን ማየት ያስፈልገናል፤ የትኛውም ነገር ጣዖት ሊሆንብን ይችላል፣ ነገር ግን ኢኮኖሚውን ለመፈጸም እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ከእርሱ እንጠጣ ዘንድ በታማኝነቱ ጣዖታታችንን ያስወግዳል፤ እንደ አምሳያው በእኛ በኩል መገለጡን በማግኘት ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም እርሱ ይጨምር ዘንድ ክርስቶስን ወደ ውስጣችን መቀበል፣ ከእኛ ጋር ማዋሐድ እና እንደ የሕያው ውኃዎች ምንጭ ከእግዚአብሔር መጠጣት ያስፈልገናል—ዮሐ. 3፡29-30።

ለ. ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልነበርን ከተገነዘብን፣ ንስሐ ልንገባ እና ልናነባ እንችላለን፣ ከዚህ ቀጥለን ግን እግዚአብሔርን በማወደስ፣ ስለ ሁሉም ነገር እርሱን በማመስገን እና እርሱን በመደሰት ከሕያው ውኃዎች መጠጣት መጀመር አለብን (1 ተሰ. 5፡16-18)፤ እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህንን ነው፤ ክርስቶስን ከመደሰታችን ውጪ እግዚአብሔር የሚፈልገው ሌላ ነገር የለም፡-

1. ከውድቀታችን የተነሣ ተስፋ እንደሌለን ልናስብ እንችላለን፤ በእርግጥ የእስራኤል ልጆችም እግዚአብሔር እንደተዋቸው እና እንዳበቃላቸው ተሰምቷቸው ይሆናል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ርኅራኄዎች አያልቁም፤ ይልቁንም በየማለዳው አዲስ ናቸው—ሰቆ. 3፡22-23።
2. እርሱን በተስፋ ለሚጠብቁት መልካም ስለሆነ ኤርሚያስ እግዚአብሔር እድል ፈንታው እንደሆነ እና እርሱን ተስፋ እንደሚያደርግም ማወጅ ችሏል፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋ አለ፣ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ተስፋ መቁረጥ የለም—ቁ. 24-25፤ ተዛ. መዝ. 16፡5፤ 73፡25-26።
3. ውድቀታችን ክርስቶስ ጽድቃችን እና ቤዛነታችን ለመሆን እንዲመጣ እንዲሁም ሕይወታችን እና የሕይወት ሕጋችን ለመሆን እግዚአብሔርን ለማወቅ እና እግዚአብሔርን ለመኖር አቅም እንዳለው ሕግ ራሱን ወደ እኛ ውስጥ ለማደሉ መንገድን ይከፍታል፤ በሌላ አነጋገር፣ የእኛ ማዕከላዊነት እና አጽናፍ-ዓለማዊነት እንዲሆን በእኛ ውስጥ እና በእኛ በኩል ከፍ ይደረግ ዘንድ ውድቀታችን ክርስቶስ ወደ እኛ እንዲመጣ በቀላሉ መንገድን ያዘጋጃል ይከፍትማል—ኤር. 23፡5-6፤ 31፡33-34፤ ቆላ. 1፡17፣ 18።
4. ዛሬ እግዚአብሔርን ካሳዘንን፣ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፤ እግዚአብሔር እኛን ለማስተካከል እና እንድንበስል እና በቀጣዩ ዘመን እንደ ድል-ነሺ ሙሽራው ወይም ለዘላላም እንደ ሚስቱ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም እንድንሆን ለማድረግ መንገድ አለው—ዕብ. 6፡1።
5. ስለ ሁኔታችን መጨነቅ አያስፈልገንም፤ እግዚአብሔር ትዕግሥተኛ፣ የሚያዝን እና የሚራራ ነው፣ እንዲሁም እኛን የበሰሉ ለማድረግ ጊዜውን ይወስዳል፡-
   ሀ. በአሁኑ ጊዜ የደከመ ወይም ጠንካራ የሆነ እያንዳንዱ አማኝ፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ክፍል ይሆናል፣ በዚያም ያለ ሁሉ የበሰለ ይሆናል—ራእ. 19፡7-9፤ 21፡2።
   ለ. ስለዚህ፣ ተስፋ መቁረጥ የለብንም፤ ይልቁንም በርኅራኄ እና በመጽናናት ሁሉ አምላክ መበረታታት እና መጽናናት አለብን—2 ቆሮ. 1፡3-4፤ ሮሜ 15፡5።
   ሐ. በውስጣችን ያለ እውነታ ይሆን ዘንድ እርሱን በመጠጣት፣ የሕያው ውኃዎች ምንጭ የሆነው የእግዚአብሔር እውነተኛ አምላኪዎች መሆን አለብን፣ ይህ በመጨረሻ እርሱ በሚሻው አምልኮ እግዚአብሔርን የምናመልክበት እውነተኛነታችን እና ልባዊነታችን ይሆናል —ዮሐ. 4፡23-24።

*© 2020 Living Stream Ministry*